ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA

የሴቶችና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
Ministry of Women and Social Affairs

Hamlin Fistula Ethiopia

UNFPA

# ትኩረት ትኩረት ለተነፈጉት

## የፊስቱላ ተጠቂዎችን ህይወት ለመታደግ የታሰበ ምሽት

አርብ ግንቦት 22 ቀን፣ 2017 በ 12:30
ሂልተን አዲስ አበባ



## የዝግጅቱ አላማ

ፊስቱላ በወሊድ ወቅት የሚከሰት አንዲት ሴት ህይወትን ወደዚህ አለም በማምጣት ሂደት ውስጥ ሊገጥማት የሚችል አስከፊ ጉዳት ነው፤ ችግሩ የሚከሰተው በተገቢው ሰአት አስቸኳይ የወሊድ አገልግሎት ካለማግኘት የተነሳ በሚፈጠር የተራዘመ ምጥ አማካኝነት ነው፤ በኢትዮጵያ ውስጥ የችግሩ ተጠቂ የሆኑ ብዙ ሴቶች ሽንትና ሰገራ የመቆጣጠር ችግር፣ እንዲሁም ረጅም ጊዜ ለሚቆይ አካላዊ ስቃይ ከመዳረጋቸዉም በላይ ለእድሜ ልክ ስነ-ልቦናዊ ችግርና መገለል ተጋላጭ ይሆናሉ፡፡

በወሊድ ወቅት የሚከሰት ፊስቱላን ሙሉ በሙሉ መከላከል ይቻላል፤ ጥራቱን የጠበቀ የእናቶች ጤና አገልግሎትን በማቅረብ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሱ አገሮች ፊስቱላን ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል መልኩ ለማስወገድ ችለዋል፤ ኢትዮጵያ ውስጥም ፊስቱላን ለማጥፋት ግዜው አሁን ነው፡፡

## የዝግጅቱ አስተባባሪዎች

**የተባበሩት መንግስታት ስነ-ህዝብ ፈንድ /ዩኤንኤፍፒኤ/፡-** ስነ-ተዋልዶ ጤናና የእናቶችን ጤና ለማሻሻል በአለም ዙሪያ የሚሰራ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ተቋም ነው፤ ዩኤንኤፍፒኤ እያንዳንዱ እርግዝና የታቀደ፣ እያንዳንዱ ወሊድ ጤናማ፣ እያንዳንዱ ወጣት አምቅ አቅሙን የሚጠቀምበት አለም እዉን ለማድረግ ይሰራል፡፡

**ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ፡-** የኢትዮጵያ መንግስት አንዱ ሴክተር ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ሲሆን በከፍተኛ ደረጃ ጥራቱ የተጠበቀ አጠቃላይ የጤና አገልግሎቶች ፓኬጅ ፍትሀዊ በሆነ መልኩ ተደራሽ መሆኑን በማረጋገጥ የህብረተሰቡን ጤናና ደህንነት የማሻሻል ተልእኮ ይዞ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

**የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፡-** የኢትዮጵያ መንግስት አንዱ ሴክተር ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ሲሆን፣ ከተልእኮ አንፃር የፆታ እኩልነት፣ የህፃናት መብትና ጥበቃ እንዲሁም ሁለንተናዊ ማህበራዊ ጥበቃ አገልግሎቶች ላይ ትኩረት በማድረግ ሴቶች፣ወጣቶች፣ ህፃናት እና ተጠቂ የህብረተሰብ ክፍሎች ከልማት፣ መልካም አስተዳደር እና ዲሞክራሲ ተጠቃሚ መሆናቸዉን ለማረጋገጥ ይሰራል፡፡

**ሀምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ፡-** በወሊድ ወቅት የሚከሰት ፊስቱላን ለማከም የሚሰራ አለምአቀፍ እውቅና ያለው ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ነው፤ በዚህ ረገድ ላለፉት ከ 60 አመታት በላይ በኢትጵያ ውስጥ የፊስቱላ ተጠቂ ለሆኑ ሴቶች የቀዶ ጥገና አገልግሎት፣ የስነ-ልቦና ስብራትን የማከም፣ ትምህርት የመስጠትና ከማህበረሰብ ጋር ዳግመኛ የመቀላቀል ድጋፍ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

ዩኤንኤፍፒኤ፣ የጤና ሚኒስቴር፣ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ሀምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ በጋራ በመሆን የጤና ሚኒስቴር አ.ኤ.አ. በ2030 በወሊድ ወቅት የሚከሰት ፊስቱላን ከኢትዮጵያ ለማጥፋት እያስተባበረ ያለዉን ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ ጥረት እዉን ለማድረግ ቁርጠኝነታቸዉን ያረጋግጣሉ፡፡ **ይህንን ጥረት ከግብ በማድረስ በኩል ቁልፍ የሚባሉ የህክምና አገልግሎቶችን ማቅረብ፣ የእናቶች ጤና አገልግሎቶችን ማጠናከር እንዲሁም የህብረተሰቡን ግንዛቤ ከፍ ማድረግ ጉልህ አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል፤ መከላከል በምንችላቸው ችግሮች የተነሳ ሴቶች አላስፈላጊ ስቃይ የማያዩባት እና ወሊድ ሁልጊዜ የደስታና ክብር ምንጭ የሚሆንባት ኢትዮጵያን ለማየት እንሻለን፡፡**

## የፊስቱላ ተጠቂ ሴቶች ምሽት

‹‹ትኩረት፣ ትኩረት ለተነፈጋቸው፡- የፊስቱላ ተጠቂዎችን ህይወት ለመታደግ የታሰበ ምሽት›› በሚል ጭብጥ ከዘንድሮው አለምአቀፍ በወሊድ ወቅት የሚከሰት ፊስቱላን የማስቆም ቀን ጋር በማያያዝ ግንቦት 22 ቀን፣ 2017 የሚካሄደው ይህ ዝግጅት የተሰሩ ስራዎችን እውቅና የመስጫ፣ መነሳሳትን መፍጠሪያ እና ቁርጠኝነትን ማደሻ ዝግጅት ይሆናል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በዝግጅቱ ላይ ትኩረት የተነፈጉ ሴቶች የጥንካሬና ፅናት ታሪኮችን በጋራ የምንዘክር ሲሆን የፊስቱላ ተጠቂ ሴቶችን ክብር፣ ጤናና ተስፋ ለማለምለም ድጋፍ እናሰባስባለን፡፡

- በወሊድ ወቅት በሚከሰት ፊስቱላ እና የማህፀን መውረድ ተጠቂ የሆኑ ሴቶችን የመለየትና ትራንስፖርት የማቅረብ ድጋፍን ጨምሮ ነፃ የቀዶ ጥገናና አጠቃላይ የድህረ ቀዶ ጥገና ክትትል አገልግሎት፤
- የተሀድሶና ስነ-ልቦናዊ ድጋፍ በማድረግ ተጠቂዎች ከማህበረሰባቸዉ ጋር እንደገና እንዲቀላቀሉ ድጋፍ ማድረግ፤
- የህይወት ክህሎትና የሞያ ስልጠና በመስጠት የተጠቂ ሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ነፃነትና ዘለቄታዊ መቋቋምን ለማረጋገጥ ድጋፍ ማድረግ፤ እና
- በወሊድ ወቅት የሚከሰት ፊስቱላ እና የማህፀን መውረድ የመሳሰሉ የእናቶች ጤና ችግሮችን ለመከላከልና የማህበረሰብ ግንዛቤን ለማሳደግ፡፡



## በዝግጅቱ የተካተቱ ዋና ዋና ጉዳዮች

- **የፊስቱላ ተጠቂዎች ምስክርነትና ታሪኮች**:- ፊስቱላን ተቋቁመው ሌሎች ችግሩ ያጋጠማቸዉን ሴቶች እንዴት እያገዙ እንደሆነ ከራሳቸው አንደበት እንሰማለን።
- **የመዝናኛና አሳታፊ ዝግጅቶች**:- በባንድ የሚቀርብ ሙዚቃ፣ የኪነ ጥበብ ክንውኖች፣ ጨረታ፣ እጣ ማዉጣት፣ ኮክቴል፣ እና ሌሎች አጓጊ ዝግጅቶች
- **ለየት ያሉ ስጦታዎች**:- ሁሉም ታዳሚዎች በፊስቱላ ተጠቂዎች በእጅ የተሰሩ የስጦታ እቃ ይበረከትላቸዋል
- **ቅርርብ መፍጠሪያ መድረክ**:- ዝግጅቱ ለድርጅትዎ ብዙ ደንበኞች ለማፍራት ምቹ የመተዋወቂያ መድረክ ይፈጥራል።
- **ለጉዳዩ ድጋፍ መስጠት**:- በዝግጅቱ ላይ በመሳተፍ ድርጅትዎ ለአንገብጋቢ ማህበራዊ ጉዳዮች የሚሰጠውን ድጋፍ ማሳየት ይችላሉ።

## የዝግጅቱ ቲኬቶች

- **የአንድ ሰው መግቢያ 20 ሺህ ብር**:- ትኬቱን በመግዛት የማይረሳ ምሽት ከማሳለፍዎ ባሻገር በኢትዮጵያ ውስጥ በወሊድ ምክንያት የሚከሰት ፊስቱላን ለማስቆም በሚደረገው ጥረት ቀጥተኛ ተሳታፊ ይሆናሉ፤
- **የፈዋሽ እጆች ድጋፍ (200 ሺህ ብር)**:- ይህ ቲኬት አንድ የፊስቱላ ተጠቂ ሴትን ህይወት በመለወጥ ረገድ ተጠቂዋን ከመለየት ጀምሮ ከቀዶ ጥገና፣ ተሀድሶና ከማህበረሰብ ጋር ዳግመኛ ከመቀላቀል ጋር የተያያዙ ወጭዎቿን በሙሉ የሚሸፍን ነው፤ ለዚህ ድጋፍዎ ሁለት የዝግጅቱ መግቢያ ትኬት የሚያገኙ ሲሆን ክብርን እና ጤናን ለመመለስ ላደረጉት ድጋፍ እውቅና ያገኛሉ።



## ተጨማሪ ድጋፍ የማድረጊያ መንገዶች

- **በድርጅት በኩል የሚደረግ ድጋፍና ስፖንሰርሺፕ**:- ድርጅቶች የዝግጅቱን አንድ ክፍል ስፖንሰር ማድረግ እና/ወይም ለጨረታና እጣ የሚቀርቡ እቃዎችን መለገስ ይችላሉ።
- **የነፃ ፍቃድ ድጋፍ**:- እያንዳንዱ የሚደረግ ድጋፍ ከፍ ያለ ዋጋ አለው፤ በዝግጅቱ ላይ በመገኘት ወይንም የዩኤንኤፍፒኤ ኦንላይን መንገዶችን በመጠቀም መለገስ ይችላሉ።
- **ሌሎች ድጋፎች**:- በዝግጅቱ ላይ ከሚቀርቡ የመዝናኛ፣ መስተንግዶና የህትመት ውጤቶች ከመሳሰሉ ነገሮች ጋር የተያያዙ ወጪዎችን ወይም የሚዲያ ሽፋንን በመደገፍ የፊስቱላ ተጠቂ ሴቶችን ለመርዳት ለመሰብሰብ የታቀደዉን ገንዘብ ከፍ ለማድረግ እገዛ ያድርጉ።



ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA

የሴቶችና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
Ministry of Women and Social Affairs

Hamlin Fistula Ethiopia

UNFPA

# ትብብርን ለማጠናከር ባዘጋጀነው ምሽት

# ኑ አብራችሁን ቁሙ

## ሂልተን አዲስ አበባ

| | | |
|---|---|---|
| አርብ<br>12:30 | 22 | ግንቦት<br>2017 |

## ትኬቶቹ በመሸጥ ላይ ናቸዉ

**የትኬት መሸጫ ቦታዎች፡-**

- ሂልተን አዲስ አበባ
- ሐምሊን ፊስቱላ ሆስፒታል
- ዩ ኤን ኢሲ ኤ
- አይ ሲ ኤስ ትምህርት ቤት (ግንቦት 9)

ኢንተርናሽናል የባንክ ካርዶችን በመጠቀም ለሚፈፀም ክፍያ ከታች ያለዉን ኪው አር ኮድ ስካን ያድርጉ

SEE THE UNSEEN



ለተጨማሪ መረጃ፣ ለትኬት ግዢ ወይም ስፖንሰርሺፕን ለተመለከቱ ጉዳዮች፡- **መሰረት ተፈሪ**

seetheunseen@unfpa.org

**091 115 7292**